# በደቡብ ጎንደር ሊቦ በአረበኛ አረጋ አሌ የሚመራው የጎበዝ አለቃ የአንድን ባንዳ ቤት ሙሉ በሙሉ አወደመ

ግንቦት 14 ለ 15 2010 ዓ.ም ምሽት ላይ በተደጋጋሚ የጎበዝ አለቆች የሚንቀሳቀሱበትን እና የአሉበትን ቦታ ለህወሃት/ ብአዴን እየጠቆመ ያስቸግር የነበር የአንድ ቅጥረኛ ባንዳ ቤት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ ሁኗል።
የደቡብ ጎንደር ዞንና የሊቦ ከምከም ወረዳ አስተዳደር የአረበኛ አረጋ አሌን የይዞታ መሬት በአካባቢው ያሉ ገበሬዎችን እርስ በርስ ለማጋጨት እረሱት እያሉ ሲያስፈራሯቸው የቆዩ ቢሆኑም የአካባቢው ገበሬዎች ግን እኛ አናርስም የወንድማችንን መሬት አንወርስም በማለት የከብቶች መዋያ ሁኖ ቆይቷል። አሁን በቅርቡ የአካባቢው ገበሬዎች ግን እኛ አናርስም የወንድማችንን መሬት አንወርስም በማለት ያቆዩትን የእርሻ መሬት ይህ ነገር አመላላሽ ባንዳ ስጡኝ እኔ እኖርበት አለሁ በማለት የቆርቆሮ ቤት ሰርቶ ለመኖር ሲዘጋጅ ከትናት በፊት ምሽት ላይ በአረበኛ አረጋ የሚመራ 20 ሙሉ ትጥቅ የታጠቀ ሀይልና 4 ጀሌዎች ያካተተው የጎነዝ አለቆች ቡድን የባንዳዎን ቤት ከበባ አድርገው ለማፈን ቢሞክሩም ባንዳው በወቅቱ ከቤት ባለመገኘቱ ከመሞት አምልጧል።

እሱን ሲያጡት በአረበኛ አረጋ የይዞታ መሬት ላይ የተሰራውን ቤት በሳት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ አድረገውት ተመልሰዋል። በዚህ የተደናገጠው ብአዴን ትናትና እና ዛሬ ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ የተውጣጣ ወታደርና ልዩ ሀይል ወደ አካባቢው መልምሎ አስታጥቆ በመላክ አካባቢውን የጦር ቀጠና አስመስሎታል።
እነ አረበኛ አረጋ አሌ በአሁኑ ሰዓት ተመልሰው ቦታቸውን ይዘዋል። በአካባቢው ያሉ ገበሬዎች እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑን ከቦታዎ የዓይን እማኞች ገልፀዋል።

ድል ለተገፋው የአማራ ህዝብ!!